# The Slide Continues: Firing at will in UDJ Camp!

(Aigaforum 07/15/09):-After advising Birtukan not to say sorry to the state and people



ዶ/ር ኃይሉ አርአያ "ከዚህ በኋላ ዝም አንልም" እነፕሮፌሰር መስፍን

በአሰግድ ተፈራና ኃይሌ ሙሉ

አንድነት ፓርቲ "ሥርዓት ጥሰዋል" ባሏቸው የአመራር አባላቱ ላይ እርምጃ መውሰዱንና ይህም እርምጃ ወደ ፊት እንደሚቀጥል፣ ማንም ከፓርቲው ህልውና በላይ ሊሆን እንደማይችል የፓርቲው ምክትል ሊቀመንበርና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ለሪፖርተር ገለፁ:: እነፕሮፌሰር መስፍን "የአንድነት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሥልጣን መባለግ" በሚል ርዕስ ባወጡት ፅሑፍ የስራ አስፈፃሚውን የአሰራር ብልሹነት "ከዚህ በኋላ ዝም አንልም" ብለዋል

of Ethiopia for her violation and disrespect of the pardon process, Prof Mesfin has been biting everyone on his way. UDJ after Birtukan is desperately looking for shelter. For some like DR Hailu Araya and Gizachew the shelter is MEDREK, a  new hodgepodge sebseb (gathering) and for some like the good old professor the shelter is simply no where…"ajewejew" camp.

Kinjit is menfes(spirit) used to be the slogan. Spirit or not the curse of the innocent Ethiopians life we lost during election 2005 is haunting these dysfunctional leaders. While aradaw Berhanu is milking Diaspora "lame bora's" for his adventure with one man dictator in Asmara and Hailu Shawel "the man" is walloping in delusion of what to do next after his right hand man in north America has basically demolished the Diaspora empire he built, the learned men of UDJ are firing at each other after cheating their young chairwoman to become a false hero!

Rumor has it the saga of kinjit the spirit will not end here...Berhanu and Andargachew have become to big to share the same lime light and wedi afom is seriously looking to corwn one of them as his main man! Expect the OLF treatment on Ginbot 7 any time soon!

For more on latest UDJ saga and the aftermath of its filtration with Medrek read below.

ዶ/ር ኃይሉ አርአያ
**"ከዚህ በኋላ ዝም አንልም"**
እነፕሮፌሰር መስፍን

በአሰግድ ተፈራና ኃይሌ ሙሉ

አንድነት ፓርቲ "ሥርዓት ጥሰዋል" ባላቸው የአመራር አባላቱ ላይ እርምጃ መውሰዱንና ይህም እርምጃ ወደ ፊት እንደሚቀጥል፣ ማንም ከፓርቲው ህልውና በላይ ሊሆን እንደማይችል የፓርቲው ምክትል ሊቀመንበርና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ለሪፖርተር ገለፁ፡፡ እነፕሮፌሰር መስፍን "የአንድነት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሥልጣን መባለግ" በሚል ርዕስ ባወጡት ፅሑፍ የስራ አስፈፃሚውን የአሰራር ብልሹነት "ከዚህ በኋላ ዝም አንልም" ብለዋል

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ "የአንድነት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በስልጣን መባለግ" የሚል "የአሉባልታ ሰነድ" ለፓርቲው አባላት አሰራጭተዋል ያላቸውን የቋሚ ኮሚቴ አባላት ከኃላፊነት አግዷል፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያምን ጨምሮ በሌሎች የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት ላይ ስለሚወስደው እርምጃ ለመምከር በመጪው ቅዳሜ ስብሰባ እንደሚካሄድም ተገለ"ል፡፡

የፓርቲው ምክትል ሊቀመንበርና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ በተለይ ለሪፖርተር ጋዜጣ እንደገለፁት የተለያዩ ኃላፊነት ያላቸው የፓርቲው አባላት ያሰራጩት ፅሑፍ በአሉባልታ ላይ የተመሰረተ፣ ችግር እንኳን ቢኖር በፓርቲው መዋቅር መሰረት ስርዓትን ተከትሎ ለመሚለከተው አካል መቅረብ የነበረበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ሐምሌ 2 ቀን 2001 ዓ.ም. "የአንድነት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሥልጣን መባለግ" በሚል ርዕስ በፓርቲው የተለያዩ ኃላፊነት ያላቸው አባላት ስም፣ የስራ ኃላፊነትና ፊርማ የተሰራጨው ፅሑፍ ፓርቲው ለሌሎች ጉዳዮች በተለይም ከመድረክ ጋር መቀላቀልን በተመለከተ ለአባላቱ መግለጫ ለመስጠት ባለፈው እሁድ በጠራው ስብሰባ ላይ የተሰራጨ ነው፡፡

በፅሑፉ መጨረሻ ስማቸውና ፊርማቸው የተቀመጠው የፓርቲው አባላት ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያምን ጨምሮ ሃያ አንድ ናቸው፡፡ የፅሑፉን

መሰራጨት ተከትሎ የፓርቲው የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰኞ እለት አስቸኳይ ስብሰባ አካሂዷል፡፡ ዶ/ር ኃይሉ እንዳሉት አራት የቋሚ ኮሚቴ አባላት ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ ተወስኗል፡፡

በትናንትናው ዕለት በተካሄደው ቀጣይ ስብሰባ ፅሑፍና ፊርማቸውን ካኖሩት መካከል የቋሚ ኮሚቴና የብሔራዊ መማክርት አባላት የሆኑትን ሳይጨምር ተመሳሳይ ከኃላፊነት የማንሳት እርምጃ መወሰዱን ዶ/ር ኃይሉ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ዶክተር ኃይሉ እንዳሉት በፕሮፌሰር መስፍንና በሌሎች የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት ላይ እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን ያለው ብሔራዊ ምክር ቤቱ ነው፡፡ ስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ የራሱን አካሄድ ያቀርባል፡፡ "የአንድነት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሥልጣን መባለግ" በሚል ርዕስ ሐምሌ 2 ቀን 2001 የተፃፈው የእነፕሮፌሰር መስፍን ጽሑፍ የፓርቲው ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከታሰሩ በኋላ ኢንጅነር ግዛቸው በወንበሩ ላይ በተጠባባቂነት ከወጡ ጀምሮ በሥራ አስፈፃሚው በኩል የተደረገው ገንቢ የሥራ እንቅስቃሴ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ይገልፃል፡፡ የፓርቲው ገንቢ እንቅስቃሴዎች አብዛኛዎቹ ስራዎች በወጣቶች የተከናወኑ እንደሆኑም ያስረዳል፡፡

የፓርቲው ዋና ፀሐፊ ሚያዚያ 13 ቀን 2001 ዓ.ም. ለአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ የተሰነዘሩ ቃላቶችን እየመነዘረ በአሽሙር የራሱን አስተያየት የሚሰጠው ይሄው መግለጫ ዋና ፀሐፊው በሰጡት መልስ ላይ ተሳልቋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከደርግ ጋር አመሳስሏቸዋል፡፡

"እነዚህ ባዕድ የምልህ አካላት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የጻፍነው ደብዳቤ የመጀመሪያውን ድራፍት አይጋ ፎረም ለተባለ ድረ-ገጽ ልከውት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ከመድረሱ ከሃያ አራት ሰዓታት በፊት ታተመ" ሲሉ ዋና ጸሐፊው ለጋዜጣው የተናገሩትን ይኸው ጽሑፍ "ምነው ራሳቸውን ቢጠይቁ" ሁሉም ነገር በጃቸው፣ ደንብንም የመሻር የፖለቲካ ውሳኔ በጃቸው" ረቂቁን በማስተላለፍ የፖለቲካ ውሳኔ አድርገው ከሆነስ ሲል ይሳለቃል፡፡

በፓርቲው ውስጥ ለተፈጠሩ ችግሮች የፖለቲካ ውሳኔ እንደሚያስፈልግ ኢንጂነር ግዛቸው ለጋዜጣው የሚቀጥለውን ተናግረው ነበር፡፡ "የፓርቲ ሕግ በጣም ጥብቅ የሆነ ነው፡፡ ይህ የፖለቲካ ሥራ እንደመሆኑ መጠን አንዳንዴ ፖለቲካዊ ውሳኔ ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ፣ ሌሎችም ይህንን እንደሚጋሩኝ አምናለሁ፣ አለበለዚያ ደንብን የጠበቀ ውሳኔ የምንለው የት ያደርሳል የሚለው

አሳሳቢ ሆኖብናል፣ ፖለቲካዊ ውሳኔ አሁን ለድርጅታችን ህልውና ወሳኝ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡"

እርሳቸው ለአውራምባ ታይምስ ለሰጡት ለዚህ አስተያየት የአሽሙር ምላሽ የሰጠው የእነፕሮፌሰር መስፍን ጽሑፍ "ማሰብ እንዲህ ነው" ደርግም እንደርስዎ ችግሮት ይሆን በፖለቲካ ውሳኔ ሰዎችን የረሸነው" እባብ የልብን አይቶ . . ". ይላል፡፡

በእነፕሮፌሰር መስፍን የተበተነው ይህ ፅሑፍ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች ጥቃቅን ጉዳዮችን አንስቶ ከስራ አስፈፃሚው ጋር ልዩነት እንዳለው ከመግለፁ ውጪ መሰረታዊ የአመለካከት ልዩነት እንዳለ አያመለክትም፡፡

"የአንድነት መጀመሪያ ዓመት ሲከበር ለበአሉ የመጡት እንግዶችና አባላት በኃይለኛ ፀሐይ ሲነፍሩ የዋሉት ድንኳን ለመከራየት ገንዘብ ባለመኖሩ መስሎን ነበር፡፡ ነገር ግን በሰኔ 20 የቃሌ ምሽት ላይ የተጋበዙት ተናጋሪ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ስለነበሩ ዝግጅቱን በኢምፔሪያል ሆቴል ለማድረግ የሥራ አስፈፃሚው ችሏል፡፡" ተብሎ የተጠቀሰው ጥቃቅን ልዩነቶች ጎልተው የተነሱ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የእነፕሮፌሰር መስፍን ጽሑፍ በመደምደሚያው ላይ እንዲህ ይላል "በሙሉ ልባቸው በሰላማዊ ትግል ዓላማችን ለማሳካት የሚጥሩ እንጂ ከትግል በፊት እጅ የሚሰጡ መሪዎችን አንሻም፣ በአባሎች መዋጮ እየኖሩ እነዚያኑ አባሎች በአደባባይ የሚወነጅሉ መሪዎችን ልናምናቸው አንችልም፡፡ የሀሳብ ልዩነትና ክርክርን እንደጦር የሚፈሩና በሀሳብ የሚከራከሯቸውን እንደ ጠላት የሚመለከቱ መሪዎች ፖለቲካ ምን ማለት እንደሆነ አልገባቸውም በካድሬነታቸው የተጫኑትን ጭፍን አሠራር ገና አላራገፉም . . . ከዚህ በኋላ ዝም አንልም" ይላል፡፡

ፕሮፌሰር መስፍን ቀደም ሲልም ሆነ አሁን ያቀረቧቸው የነበሩት መረጃዎች መሰረት የሌላቸው እንደነበሩ፣ በአሉባታዎች ላይ ሳይገኙ በስብሰባ በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ በተላለፈባቸው ጉዳዮች ላይ ዘግይተው የተቃውሞ አስተያየት መሰንዘር የተለመደ ተግባራቸው እንደሆነ ያስረዱት ዶ/ር ኃይሉ አንዳንድ የፓርቲው አባላት "እናከብርዎታለን፣ እንወድዎታለን፣ ነገር ግን እየተሰራ ያለው ስራ ትክክል አይደለም በሚል በተደጋጋሚ ቢገልጹላቸውም እሳቸው ግን ስህተታቸውን ማረም አልቻሉም" ብለዋል፡፡

"በተደጋጋሚ ጥፋት ከሰሩ ለምን እርምጃ አትወስዱም? እሳቸውን

ትፈራላችሁ?" በሚል ከሪፖርተር ለቀረበላቸው ጥያቄ "አንፈራም፡፡ የምንፈራበት ምክንያት የለም፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ቢሆኑ ኖሮ ሰኞም ሆነ ዛሬ አስፈላጊው እርምጃ ይወሰድባቸው ነበር" በማለት ዶ/ር ኃይሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ አያይዘውም "ፕሮፌሰር መስፍን የታወቁ፣ ኢትዮጵያን ያገለገሉና ለአገራቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉ የምናከብራቸው ግለሰብ ናቸው በሚል እስከ አሁን ቆይተናል፡፡ ወደፊት ግን ብሔራዊ ምክር ቤቱ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል ብለን እናምናለን" ብለዋል፡፡

ዶ/ር ኃይሉ እንዳሉት የልዩነቱ መሰረት የሆነው ከመድረክ ጋር አብሮ ለመስራት የተጀመረው ግንኙነት ይቀጥላል፡፡ አንድነት ፓርቲ ጠንካራ ሆኖ በጥንካሬው ሳይመካ ከሌሎቹም አጋር ፓርቲዎች ጋር አብሮ እየሰራ እንደሚገኝ የገለፁት ዶ/ር ኃይሉ ለሚቀጥለው ምርጫም ሆነ ከምርጫው በኋላ ላለው እንቅስቃሴ በሕብረት የመስራት ባህል ለፓርቲው የበለጠ ኃይልና ጥንካሬ እንደሚሰጠው አመልክተዋል፡፡

Last Updated ( Wednesday, 15 July 2009 )